# ጀግንነትና ትግል እንደ አማራ፣ድርጅት እንደሞረሽ፣መሪ እንደተክሌ የሻው

**“ለማንነታችን መከታ ያልሆነን፣ለመጠቃታችን ምክንያት እየሆነ ነው” በሚል ርእስ በሞረሽ ወገኔ የአማራ ድርጅት ጃንዋሪ2 2017ዓ.ም.የወጣው መግለፃ** ከግንቦት 7 ውሸት ቋቱ መሪያቸው ከእርቃኑ(ብርሀኑ) ነጋ ጀምሮ ደናቁርት ተከታዮቹን ከኢሳት ጭምር ሲያንጫጫ ከርሟል።

ከሥምንት ዓመታት በላይ የዋሹት  የውሸት ክምር **በአንዷት እጥር ምጥን ያለች፣ ዕውነትን ሥንቋ ያደረገች የሞረሽ መግለጫ** ዝርክርካቸው ለመውጣት በመብቃቱ፣በተወዳጁና በታዋቂው  የሞረሽ ሊቀ መንበር ላይ ለምን ዕውነት ተነገረብን፣ለምን ቁሥላችን ተነካብን በሚል ተስፋ መቁረጥ የሥድብ ነጎድጓድ ሲጥሉና ሲንከባለሉ ከርመዋል።

የሥድቡና የአሉባልታውም ዋና ዓላማ ሞረሽ በፅኑ መሠረት የተገነባ ሥለሆነ አልተሳካላቸውም እንጅ ሞረሽን ለመከፋፈል ነበር። ለወደፊትም ከቻሉ በአማራው መካከል ጣልቃ በመግባት ለመከፋፈል  መጣራቸው አይቀሬ ነው ።

ምናልባት ቆርጠው በአማራነት መቆም የተቸገሩትን፣እንደውሀ ቀጅ ከአንዱ ድርጅት ወደሌላው ግን በሁለት ቢለዋ ለመብላት የሚፈልጉትን (አንዳንድ የሥራ እንቅፋት የሚሆኑ፣ጆሮ ጠቢዎች ኑረውም የማይጠቅሙን ሥለሚኖሩ፣እነርሱን ቢወስዱልን ደስታውን አንችለውም) ያገኑ ይሆናል እንጅ  በአማራ ማንነት ጥያቄ መቶ በመቶ አምኖ የቆመውን፣ገንዘቡን፣ጉልበቱን፣ጊዜውንና ዕውቀቱን የሰጠውን የሞረሽ ደጋፊና አባል ቢሞክሩት አፀፋውን እንደሚመልስ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል።  ዕድሜ ለሞረሽ ፣ዛሬ ሁላችንም በሚገባ ነቅተናል። ምክንያቱም

**(1ኛ)** የሞረሽ ሊቀመንበር ቀደም ሲል በድርጅቱ ሳይሆን በግሉ የፃፋቸውን ትምህርታዊ መፃሕፍት በማንበብ፣

**(2ኛ)** ሞረሽ በየጊዜው ያወጣቸውን መግለጫዎችና ምፅአተ አማራ መፅሐፍን በማንበብ፣

**(3ኛ)** የምናከብረውና የምንወደው የሞረሽ ሊቀመንበር **ተክሌ የሻውም** በአጭር ጊዜያት ውስጥ ሁለት(2)ጊዜ፣ በአገራት በመዘዋወር አባላቱንና ደጋፊዎችን አነቃቅቶ፣ታሪክን አሥመርኩዞ ትምህርትና ንቃት በመሥጠቱ፣

**(4ኛ)** የአማራውም የማንነት ጥያቄ ደምሥራችን ውስጥ በመግባቱ፣

**(5ኛ)** የሞረሽን ሊቀ መንበር  የታሪክ ዕውቀት፣ታታሪነት፣አስተማሪነት፣ደከመኝ ታከተኝ ሳይል ሁለመናውን ለአማራው ማንነትና ህልውና የሰጠ ዕውነተኛ አማራ ኢትዮጵያዊ እንደሆነ  በማረጋገጣችን፣

**(6ኛ)** አሁን በቅርብ ጊዜ የተቋቋመውንም ኢትዮጵያ የሚደርስ የራዲዮን  አገልግሎት ሥናጤን፣

**(7ኛ)** ሞረሽ  አመራሩን ሠፋ ባለቦርድ ከማዋቀሩም ባሻገር፣የራዲዮኑንም ቦርድ በተመለከተ  እንደዚሁ አድርጎ መንቀሳቀሱ በተክሌና በመሰሎቹ ላይ ያለንን ዕምነትና አብሮነት ሊያሥተሳስረው በቅቷል፣ እኛም በማንም የወሬ ጋጋታ የማንፈታ “ወይ ፍንክች የአባ ቢለዋ ልጅ” ሆነናል።

ግንቦት 7 ሲነሳ መቼም ብርሀኑ(እርቃኑን የቀረው) ነጋ  አይቀሬ ነው።ከሥምንት ዓመታት በላይ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሌለውን እንዳለው እያደረገ በኢሳት አማካይነት ሲዋሽ ቢኖርም  “ቢከፍቱ ተልባ” መሆኑንና  ዕርቃኑን መቅረቱን በአማራ ማንነት ጎንደር ላይ የፈነዳው የሕዝብ አመፅና ከዚያም ተከትሎ የተደረገው በቂ ምስክር ነው።

ከዚያም በኋላ ውድቀታቸውን ለመሸፈን የአማራውን የማንነት ጥያቄ ለመጥለፍና እኛ ነን ለማለት ያላደረጉት አይን አውጣነት አልነበረም።አሁን ደግሞ በቅርቡ ባዶነታቸውን በራሳቸው በነዓምን ዘለቀ ሠምተውታል።

የእርቃኑ ነጋ ደናቁርት ይህንንም መርዶ እየሰሙ “ከአፈርኩ አይመልሰኝ” ብለው ይሁን ወይም ምናዓይነት ያፍዝ አደንግዝ ቀውስ ውስጥ ወድቀው ይሁን ባልታወቀ ምክንያት፣ እሥከዛሬዋ ዕለት ድረስ ፖለቲካን በሥድብ ተክተው የዕውር የድምብሩን  ሽምጥ ሲጋልቡ ይሥተዋላሉ። መነሻውን ያላወቀ መድረሻውንም ሊያውቅ አይችልም።

ኢሳት የብርሀኑን ነጥ ውሸት  የቀረፈ መሥሎት ብርሀኑ  ወታደር እንዳለው እንዲመስል በመጨነቅ ይመስላል፣ የአማራውን ተጋድሎ፣የነፃነት ኃይሎች እያለ ወሬ ሲለቅ ከርሟል። አሁን  ይህ ውሸት አያልቅበት እርቃኑ ነጋ  “ የነፃነት ኃይሎች እኛ ነን” ብሎ የመጨረሻውን የማጭበርበሪያ ካርድ መዞ ብቅ ብሏል። “ዕውነትና ንጋት እያደር ይጠራል” እንደሚባለው፣የዚህ ፀረ አማራው ብርሀኑ ነጋ ጉዳይ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ሥለደረሰ የአማራውን ትግል እያጠናከርን በሄድን ቁጥር ብርሀኑና ደናቁርቱ ከእነሥድባቸው ወደመቃብራቸው ይገባሉ።

የሞረሽን ሊቀመንበር የተክሌ የሻውን ሥም እያነሱ የሚያብጠለጥሉትን ደናቁርት የምንነግራቸውና የምንላቸው  ቢኖር፣

(1) እንደተክሌ የሻው ታሪክ ዕወቁ፣

(2) እንደተክሌ የሻው አፃፃፉን እወቁ።በአንዷት አጭር ፅሁፍ ውጥቅጣችሁን ያወጣው አፃፃፍ በመቻሉ እንደሆነ እመኑ፣እጅ ሥጡ።

(3) ብርሀኑ እነኃይሉ ሻወልን እና እነልደቱን እየተሳደበና እያራከሰ ብርሀኑ ለብርሀኑ እንደፃፈው መፅሐፍ ተብዬው ሳይሆን፣እንደተክሌ የሻው ራስን ለሕዝብ አሳልፎ ሰጥቶ ለሕዝብ የሚጠቅም መፃሕፍት መፃፍ ያሻል፣

(4) ዛሬ አማራው  ለማንነቱና ለህልውናው በሚዋደቅበት ወቅት፣”አማራና ትግሬ”፣ኦሮሞን እንደሚጨቁኑት አድርጎ ኦነግ ለአውሮፓ ህብረት አቤት ሲል ጀግናው ተክሌ የሻው ሁኔታውን ተከታትሎ ዕውነታውን ለአውሮፓ ህብረት በማቅረብ የኦነግን  ቅጥፈት መክቷል።

(5) ለተባበሩት መንግሥታትም አማራውን የገደሉና ያሥገደሉ ወንጀለኞችን በዓለም ፍርድ ቤት ለማቅረብ ሥርዓትንና ደንብን የተከተሉ በማሥረጃ የተደገፉ ጽሁፎች ያቀረበ ሰው ነው።

ይህንን እሥከዛሬ ድረስ  ከእነፕሮፌሰር አሥራት በሥተቀር አማራም ሆነ የአማራ ድርጅት ነኝ የሚል አቅርቦና ድምፁን አሠምቶ አያውቅም። እንደውም የብርሀኑ ደናቁርትና አብረዋቸው ላይ ታች የሚሉ አንዳንድ የአማራ ድርጅት ተወካይ አማራ ነን ባዮች “ተክሌ የሻውን በፌስቡክ እና

በፓልቶክ ጭምር በሰድብ ከተቀበልነው፣ሞረሽ ይዳከማል ፣የሞረሽ መዳከም ደግሞ የአማራውን ተግል ያዳክምልናል" ብለው ያስባሉ። ነገር ግን ዕውነታው ሌላ ነው። ሞረሽ ለፀረ አማራ ኃይሎች እንደማይበገርና ይበልጥ እንደተጠናከረ በተግባር አሳይቷል።

ብርሀኑ(እርቃኑ) ነጋ በየሄደበት ተገንጣዮችን እነኦነግን እየጎተተ "ግንጠላውን አፋጥኑላቸው፣እኔንም ከወያኔ ጋር አሥታርቁኝና የጠማኝን ሥልጣን ልያዝ " ለማለት በአውሮፓ ህብረት፣በአሜሪካ ወዘተ እየዞረ ቱልቱላውን ነፍቶ ይመጣል እንጅ ፋይዳ ያለው ነገር አይሠራም።

ለእነዚህ የግንቦት7 ጀሌዎችና መሰሎቻቸው ያለኝ ምክር የሚከተለው ነው። "የሞረሽን ሊቀመንበር እሥከዛሬ በመሳደብ ሥድአደግነታችንንና ጋጠወጥነታችንን መመሪያችን አድርገን ነበር፣ይህም ሞረሽን የበለጠ አጠናከረው እንጅ አላዳከመውም። እኛን ግን ከባዶነታችን በተጨማሪ ቀውስ በቀውስ አድርጎናልና ይቅርታ እየጠየቅን ከዛሬ ጀምሮ የሞረሽ ደጋፊዎች መሆን እንፈልጋለን" ብላችሁ ወደሞረሽ ብትቀርቡ ምህረት ያደርግላችኋል። አማራ ለምህረት የታወቀ ነው።

የአማራ ማንነትና ህልውና በትግላችን ተግባራዊ ይሆናል

ሸንቁጥ በላቸው